## የJB-R1 ፖሊሲ:- የአድሎ ወይም ትንኮሳ/ጥቃት የተማሪዎች አቤቱታ ምርመራ ደንቦች

የዴንቨር የሕዝብ ት/ቤቶች ("ዲስትሪክቱ") ሕገ-ወጥ ከሆነ መገለል እና ጥቃት/ትንኮሳ የፀዳ የትምህርት ከባቢ ያቀርባል። ዲስትሪክቱ ስለ ሕገ-ወጥ የሆነ መገለል እና ጥቃት/ትንኮሳ ያሉ ስጋቶችን እና አቤቱታዎችን በአፋጣኝ ያጣራል፣ ሕገ-ወጥ የሆነ መገለል እና/ወይም ጥቃት/ትንኮሳ ድርጊት ተፈፅሞ ሲገኝም እርምጃ ይወስዳል፣ በአጥፊዎች ላይም እንደ ጉዳዩ ሁኔታ ተገቢ ቅጣቶችን ይጥላል፣ እንዲሁም በስቴት እና ፌደራል ሕጎች በሚያዙት መሠረት ሕገ-ወጥ የሆነ መገለል እና/ወይም ጥቃት/ትንኮሳን በማጋለጥ የተሳተፉ ግለሰቦችን ሁሉ ሚስጥርና ደህንነት ይጠብቃል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም፣ አቤቱታው እንዲጣራ ወደ ሕግ አካል ይላካል።

ሕገ-ወጥ የሆነ መገለል እና/ወይም ጥቃት/ትንኮሳ የሚቀርቡ ስጋቶችን እና አቤቱታዎች በአፋጣኝ እና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ለማስተናገድ ዲስትሪክቱ የሚከተሉትን የአሰራር ደንቦች አጽድቋል። አቤቱታዎች በጽሑፍ ወይም በቃል ሊቀርቡ ይችላሉ።

### ትንታኔዎች

1. "የተማሪ ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ" ማለት ስለተጠረጠሩ ሕገ-ወጥ  መገለል እና ጥቃት/ትንኮሳ አቤቱታዎችን/ክሶችን የሚቀበል የተማሪዎች አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ወይም የወከሉት ተዋካይ ማለት ነው።

2. "ቅሬታ አቅራቢ ግለሰብ" /"Aggrieved Individual"/ ማለት ከ18 ዓመት በታች የሆነው እና በቀጥታ ጉዳት የደረሰበት እና/ወይም አድሎ እና ጥቃትን/ትንኮሳን የሚከለክሉ የቦርድ ፖሊሲዎች ጥሰት ምስክር የሆነ ተማሪ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ወይም ከ18 ዓመት በላይ የሆነ እና በቀጥታ ጉዳት የደረሰበት እና/ወይም አድሎ እና ጥቃትን/ትንኮሳን የሚከለክሉ የቦርድ ፖሊሲዎች ጥሰት ምስክር የሆነ ተማሪ ማለት ይሆናል።

3. "ጥቃት/ትንኮሳ" ማለት በግለሰብ ጥበቃ-በተደረገለት መደብ /Protected Class/ አቋም ላይ የተነጣጠረ ማንኛውም ተቀባይነት የሌለው፣ ተስማሚ ያልሆነ እና አናዳጅ የቃል፣ የጽሑፍ ወይም የአካል ባሕርይ ሲሆን የሚከተሉትን ሊያስከትል የሚችል ነው፡-  (1) አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ ወይም አዕምሯዊ ጉዳት፣ ወይም በንብረት ላይ አደጋ የሚያደርስ (2) አንድ ግለሰብ በትምህርት ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ ውስጥ ከመሳተፍ ወይም ከመጠቀም ለማገድ የሚደርስ በበቂ ሁኔታ ከባድ፣ ጽንዑ ወይም ጎልቶ የሚታይ የሆነ፣ ወይም አሸማቃቂ፣ ተስማሚ ያልሆነ፣ ወይም አስፈሪ ከባቢ የሚፈጥር፣ ወይም (3) የት/ቤቱን መደበኛ ትግበራ በከፍተኛ ሁኔታ የሚያደናቅፍ

   ሀ. ጥቃት/ትንኮሳ ብዙ ዓይነት ቅርጽ ሊይዝ ይችላል። በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡-
      i. የቃላት ስድቦች እና ስም-መጥራት፣
      ii. ሞባይል ስልክን ወይም ኢንተርኔትን በመጠቀም ሊደረጉ የሚችሉ የንድፍ/ስዕል እና የጽሑፍ መግለጫዎች፣ እና/ወይም
      iii. ሌሎች አካላዊ ማስፈራራት፣ ጉዳት፣ ወይም አዋራጅ ባሕርያት።

### የተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ ተግባራት

የተማሪ ደንብ ማክበር ጽ/ቤት ኃላፊ ምርመራ የማካሄድ እና ሕገ-ወጥ አድሎን እና ጥቃትን/ትንኮሳን የሚከለክሉ የፌዴራል ወይም የስቴት ሕጎች ወይም የቦርድ ፖሊሲዎች ጥሰት ጥርጣሬ ዙሪያ ሁሉንም አቤቶታዎችን የማስተናገጃ ደንቦችን እና ሂደቶችን የማስተባበር ኃላፊነት አለበት።

ል

የዲስትሪክቱ የተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ አድራሻ፡-

ዋና ሥራ አስፈፃሚ
የተማሪዎች አገልግሎት
ዴንቨር የሕዝብ ት/ቤቶች
1860 Lincoln St.
Denver, CO 80203
ሥልክ ቁጥር፡- 720-423-3437

**የተከለከሉ የፆታ ጥቃቶች**

ተቀባይነት የሌላቸው የፆታ ቀረቤታዎች፣ የፆታ ውለታ ይያቄዎች፣ ወይም ሌላ የፆታ ጥቃት/ትንኮሳ ባህርይ የተላበሰ የቃል፣ የድርጊት፣ ወይም የአካላዊ ጥቃቶች/ትንኮሳዎች፤ ጥቃት የሚደርስበት እና ጥቃት አድራሹ ተማሪዎች አንድ ዓነት ፆታ ያላቸው ቢሆኑም ባይሆኑም፣ እንዲሁም ጥቃት የደረሰበት ሰው ጥቃቱን ቢቃወመው ወይም ቢቀበለውም፣

1. መቀበሉም በግልጽም ሆነ በስውር፣ ወይም የተማሪው በትምህርት ፕሮግራም ወይም ተግባር ውስጥ ለመሳተፍ ቅድመሁኔታ ሲሆን፣
2. እንዲህ ዓይነት ባሕርይን መቃወም የተቃወመውን ተማሪ ትምህርት ላይ ጉዳት የሚያመጡ ውሳኔዎችን ለመወሰን ምክንያት ሲሆን፣
3. እንዲህ ዓይነት ባሕርይ ከፍተኛ/አደገኛ፣ ተደጋጋሚ ወይም ጉልህ የሚባለው የአንድን ተማሪ በትምህርት ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ የመሳተፍ ወይም የመጠቀም አቅም ሲገድብ ወይምም ምቹ ያልሆነ ወይም አጸያፊ/አስከፊ የትምህርት ከባቢ ሲፈጥር ነው። የአንድ-ጊዜ ክስተት እንደ ጥቃት ተደርጎ ለመቆጠር ከፍተኛ/አደገኛ መሆን አለበት።

በተማሪ ሠራተኛ ላይ ወይም በሠራተኛ ተማሪ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ፆታዊ የወነ ባሕርይ ተቀባይነት የሌለው እና ፆታዊ ጥቃት/ትንኮሳ ተደርጎ ይወሰዳል።
ፆታን መሠረት ያደረገ ነገር ግን ፆታዊ ባሕርይንነት የሌለው ማንኛውም የቃላት ስድብ፣ ወይም የአካል ትንኮሳ፣ ማሸማቀቅ ወይም ጥላቻ እንደ ፆታዊ ጥቃት ተደርጎ ይወሰዳል።

የፆታዊ ጥቃት/ትንኮሳ ከላይ እንደተተነተነው በእነሱ ብቻ ባይወሰንም የሚከተሉትን ያካትታል፡-

1. ፆታ-ነክ የቃላት "ሹፈት"፣ ጉዳት ወይም ጥቃት፣
2. ለወሲባዊ ድርጊት ግፊት ማድረግ
3. ፆታዊ ወይም ወሲባዊ ትርጓሜ ሊሰጣቸው የሚችሉ ተደጋጋሚ አስተያየቶች፣
4. እንደ መታ-ማድረግ፣ መቆንጠጥ፣ ወይም ተደጋጋሚ አካላዊ መተሻሸት ያሉ ተቀባይነት የሌላቸው መነካካቶች፣
5. ስውር ወይም ግልጽ የውጤት ማስፈራሪያን ወይም የግል ጥያቄዎችን፣ ወይም የፆታ ጥቃትን ያዘለ የፆታዊ/ወሲባዊ ግብዣ ማቅረብ ወይም መጠየቅ።
6. ላላ

**የአቤቱታ አቀራረብ ደንብ**

ተበዳይ ግለሰብ የገጠመውን/የገጠማትን ክስተት/ገጠመኝ የAC-E2፡- አድሎ/ጥቃት/ትንኮሳ ማሳወቂያ ቅጽን በመጠቀም ለአስተዳዳሪ፣ ለአማካሪ (ካውንስለር)፣ ለመምህር፣ ወይም ለዲስትሪክቱ የደንብ ማክበር ጽ/ቤት ማሳወቅ አለበት/ባት። መምህራን፣ አማካሪዎች፣ ርዕሰ መምህራን፣ ወይም የዲስትሪክቱ ሠራተኞች የደረሳቸውን ሁሉንም ሪፖርት ወዲያውኑ ለተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ማስገባት አለባቸው። የተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ በተከለከለው ድርጊት ውስጥ ተሳታፊ ነው ተብሎ የተጠረጠረ ከሆነ አቤቱታው ለዋና ተቆጣጣሪው ሪፖርት ይደረጋል፣ ዋና ተቆጣጣሪውም ተለዋጭ የተማሪ ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ ጉዳዩን እንዲመረምር ይሰይማል።

ማንኛውም ተበዳይ ግለሰብ ዲስትሪክቱን፣ ሌላ ተማሪን ወይም ማንኛውንም የት/ቤት ሠራተኛ ሕግ-ወጥ በሆነ የአድሎ ወይም ጥቃት/ትንኮሳ ድርጊት በመክሰስ ለተማሪ ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት አቤቱታ/ክስ ማስገባት ይችላል። አቤቱታዎች/ክሶች በጽሑፍ ወይም በቃል ሊቀርቡ ይችላሉ። የጽሑፍ አቤቱታ/ክስ ማስገባት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የAC-E2፡- አድሎ/ጥቃት/ትንኮሳ ማሳወቂያ ቅጽን እንዲጠቀም እናበረታታለን።

ሁሉም አቤቱታዎች/ክሶች የክሱን ክስተት፣ የተከሰተበት ቀን እና በክስተቱ የተሳተፉ ሰዎች ስም(ሞች)፣ ምስክሮች ካሉም ምስክሮችን ጨምሮ ዝርዝር መግለጫዎችን ማካተት ይኖርባቸዋል። አቤቱታው/ክሱ ክስተቱ ከተከሰተ በኋላ በተቻለ ፍጥነት ሪፖርት መደረግ ይኖርበታል።

የተማሪ ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ የክሱን መሠረታዊ ምክንያት በግልፅ ለመረዳት ይችል ዘንድ ጉዳት የደረሰበት ግለሰብን ወይም በሕገ-ወጥ አድሎ ወይም ጥቃት የተከሰሰው ግለሰብን በተቻለ ፍጥነት ያነጋግራል፤ ነገር ግን ዲስትሪክቱ ክሱን/አቤቱታውን ከተቀበለ ከ15 የትምህርት ቀናት ማለፍ የለበትም።

የተማሪ ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ ከጉዳት የደረሰበት ግለሰብን እና/ወይም በሕገ-ወጥ አድሎ ወይም ጥቃት የተከሰሰው ግለሰብን ጋር የመጀመሪያ ስብሰባ ካደረገ በኋላ ስለክሱ ምላሽ ለማግኘት በተከለከለ ድርጊት ተሳትፏል የተባለ ተማሪን፣ የእሱን/የእሷን ወላጆች/አሳዳጊዎች ያነጋግራል። እነዚህ ሰዎች አመለካት ሙሉ እና ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት ወይም ክሱን ለመፍታት አስፈላጊ ስለሆኑት ክሶች በሙሉ በተማሪ ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ ሊነገራቸው ይገባል።

በመጀመሪያዎቹ ስብሰባዎች ላይ የተማሪ ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ ስለኢ-መደበኛ እና መደበኛ እርምጃዎች አወሳሰድ ሁኔታዎች፣ ስለክሱ ሂደት፣ እንዲሁም ከሳሽም ሆነ ተከሳሽ ግለሰቦች በማንኛውም ጊዜ ከኢ-መደበኛው ሂደት መውጣት እና ወደመደበኛው የክስ ሂደት መግባት መብት አላቸው። የተማሪ ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ ከሳሽ ክለሰብ ክሱን በጽሑፍ ማስገባቱን ወይም አለማስገባቱን ወይም እርምጃ የሚጠይቅ መሆኑን አለመሆኑን፣ ዲስትሪክቱ ሕገ-ወጥ አድሎን ወይም ጥቃትን/ትንኮሳን ለማረም እርምጃ ለመውሰድ፣ እንዲሁም ተደጋጋሚ ሕገ-ወጥ አድሎ፣ ጥቃት/ትንኮሳ፣ ወይም እንዲህ ዓይነት ድርጊቶችን ሪፖርት ያደረገ ወይም በምርመራ የተሳተፈ ግለሰብ ላይ በቀልን ለመከላከል በሕግ እንደታዘዘ መግለጽ አለበት። የተማሪ ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊው ዲስትሪክቱን በተከለከሉ ባሕርያት ላይ በሚገባ ምላሽ ከመስጠት እና ወደፊትም እንዳይከሰቱ ከመከላከል የማያግደው እስከሆነ ድረስ ሚስጥር እንዲጠበቅ መጠየቅ ተቀባይነት እንደሚኖረው መግለጽ ይኖርበታል።

**ኢ-መደበኛ እርምጃ /Informal Action/**

ተበዳይ ግለሰብ እና/ወይም የማይፈቀድ ስነ-ምግባር ተሳትፏል የተባለው ግለሰብ ጉዳዩ በኢ-መደበኛ መንገድ እንዲፈታ ከጠየቁ እና/ወይም የተማሪዎች ደንብ ማክበር ጽ/ቤት ኃላፊ ጉዳዩን በኢ-መደበኛ መንገድ መፈታት የሚችል መሆኑን ካመነበት፣ የተማሪዎች ደንብ ማክበር ጽ/ቤት ኃላፊ ጉዳዩን በሽምግልና፣ በምክር ወይም በሌሎች ስነ ሥርዓታዊ መንገዶች ለመፍታት ይሞክራል። በእንዲህ ዓነት የኢ-መደበኛ መንገድ ተፈትቷል ብለው ሁለቱም ወገኖች ካመኑ ምንም ሌላ ተጨማሪ የደንብ ማስከበር እርምጃ አይወሰድም። የትኛውም ወገን የሕገ-ወጥ አድሎ ወይም ጥቃት/ትንኮሳ ክስ በኢ-መደበኛ መንገድ ለመፍታት አይገደድም፤ እናም የትኛውም ወገን በማንኛውም ሰዓት የኢ-መደበኛ ሂደቱ እንዲቆም መጠየቅ ይችላል። ኢ-መደበኛ የሆነ የአፈታት መንገድ በት/ቤቱ ሠራተኞች የቀረበ ክስ ሂደትን፣ እንዲሁም ጥፋቱ በወሲባዊ ትንኮሳ ወይም በሌላ ደንብ የተላለፉ ተማሪዎችን ክስ ለመፍታት ጥቅም ላይ አይወልም።

**መደበኛ እርምጃ**

የኢ-መደበኛ አፈታት መንገድ ተገቢ ካልሆነ፣ የማይቻል ከሆነ፣ ወይም ስኬታማ ካልሆነ፣ የተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ በክሱ የቀረበው የሕገ-ወጥ አድሎ ወይም ጥቃት/ትንኮሳ ስለመፈጸሙ/ስላለመፈጸሙ እና/ወይም በምን ያህል ደረጃ

እንደተፈጸመ ይመረምራል። የተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ የሕግ-ወጥ አድሎ ወይም ጥቃት/ትንኮሳ ስለመፈጸሙ/ስላለመፈጸሙ በማጣራት ሂደት የሚከተሉትን መረጃዎች ሊጠቀቀም ይችላል፡-

1. በክሱ ስለቀረበው ክስተት የማንኛውንም ምስክር ገለጻዎች፣
2. በድርጊቱ ስለተሳተፉ አካላት ተዓማኒነት ማስረጃ፣
3. ተከሳሽ ግለሰቡ በተባለው የተከለከለ ባሕርይ ውስጥ ተሳትፎና በሌሎች ላይ የተከለከለ ባሕርይን ፍጽሞ ስለመገኘቱ ወይም አለመገኘቱ ማስረጃ፣
4. የተባለው ክልክል ስነ ምግባርን ተከትሎ የተበዳይ ግለሰብ እና/ወይም የተከሳሽ ግለሰብ ግብረ-መልስ ወይም የባሕርይ ለውጥ ማስረጃ፣
5. ተከሳሽ ግለሰብ እና/ወይም ተበዳይ ግለሰብ እንዲያ ዓይነቱን ባሕርይ ለመቃወም እርምጃ ስለመውሰዳቸው - አለመውሰዳቸው መረጃ፣
6. በጉዳዩ ተሳታፊ ወገኖች ያቀረቧቸው ማስረጃዎች ወይም ምስክሮች መግለጫዎች፣
7. ሌሎች በወቅቱ የነበሩ/የታዩ ማስረጃዎች፣ እና/ወይም
8. በተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ አግባብነት አላቸው የሚባሉ ማስረጃዎች።

አንድን ድርጊት ወይም ባሕርይ የሕግ ወይም የፖሊሲ ጥሰት ነው ብሎ ለመወሰን የተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ የሚከተሉትን ጭምሮ ሁሉንም አግባብነት ያላቸውን ጉዳዮች መመልከት አለበት፡-

1. ጥፋቱ የአንድን ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተማሪዎችን ትምህርት ምን ያህል የሚጎዳ መሆኑን፣
2. የጥፋቱ ዓይነት፣ ድግግሞሽ፣ እና ጊዜ ርዝመት፣
3. ባልተፈቀደ ባሕርይ ተሳታፊ/ተከሳሽ የተባለው ግለሰብ እና ተበዳይ ግለሰብ እና/ወይም ጥቃቱ የደረሰበት ግለሰብ ማንነት እና ግንኙነት፣
4. ባልተፈቀደ ባሕርይ የተሳተፉ ተከሳሽ ግለሰቦች ቁጥር እና የዚህ ባሕርይ ተተቂ የሆኑ ተማሪዎች ቁጥር፣
5. ባልተፈቀደ ባሕርይ ተሳታፊ/ተከሳሽ የተባለው ግለሰብ እና ተበዳይ ግለሰብ እና/ወይም ጥቃቱ የደረሰበት ግለሰብ እድሜ፣
6. የት/ቤቱ ስፋት፣ ክስተቱ የተፈጸመበት አካባቢ እና ሊከሰት የቻለበት ሁኔታ ወይም አውድ፣ እና/ወይም
7. በት/ቤቱ የተከሰቱ ሌሎች ክስተቶች።

የተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ ግኝቶችን እና የመፍትሄ ሀሳቦችን የያዘ የጽሑፍ ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት። ሪፖርቱም በተማሪዎች እና/ወይም በሠራተኞች ላይ ተገቢ የሆነ እና ተጎጂ ግለሰቡን የሚደግፍ የስነ ምግባር/የስነ ሥርዓት እርምጃ የሚያካትት ሲሆን ገቢ የሚደረገውም ለዋና ተቆጣጣሪው ወይም ለተወካያቸው ነው። ገቢ መሆን ያለበትም የተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ ከአቤቱታ አቅራቢው/ካሳሹ ጋር የመጀመሪያውን ስብሰባ ካደረገበት 15 የትምህርት ቀናት በኃላ፣ ወይም የኢ-መደበኛ አፈታት ሂደት መቆምን አስከትሎ 15 የትምህርት ቀናት በኋላ ይሆናል። ተማሪዎች ላይ የተነጣጠረ የወሲባዊ ጥቃት ባሕርይ ያለው ድርጊት እንደ አግባብነቱ የህፃናት ብዝበዛ ተደርጎ በሚመለከተው አካል አግባብነት ያለው ሕግ እና የቦርድ ፖሊሲ በሚፈቅደው መሠረት እንዲመረመር ሪፖርት ይደረጋል። የተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ የፌደራል እና የስቴት ሕጎች በሚፈቅዱት መጠን እና የተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ ውሳኔን ተከትሎ በጉዳዩ የተሳተፉ ተማሪዎች ወላጆችን/አሳዳጊዎችን ጨምሮ ለሁሉም ወገኖች ስለምርመራው ሂደት እና በዲስትሪክቱ ስለተወሰዱ እርምጃዎች በ5 ቀናት ውስጥ ማሳወቅ አለበት። ዲስትሪክቱ በተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ ሪፖርት ውስጥ የሚገኙትን የመፍትሄ ሃሳቢችን ማስፈጽም አለበት።

ተበዳይ ግለሰብ እና/ወይም ተጠርጣሪው ወንጀለኛ ግለሰብ በተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ ግኝቶች እና የመፍትሄ ሃሳቦች ባይስማሙ፣ ተበዳይ ግለሰብ እና/ወይም ተጠርጣሪው ወንጀለኛ ግለሰሰብ የተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ ውሳኔ እንደገን እንዲታይላቸው የምርመራው የመጨረሻ ውጤት ማሳወቂያው ከደረሳቸው ጀምሮ በ10 የካላንደር ቀናት ውስጥ ለዋና ተቆጣጣሪው ወይም ለተወካያቸው በጽሑፍ ማመልከቻ ይግባኝ ሊሉ ይችላሉ። የጽሑፉ ይግባኝ ማመልከቻ ተጨማሪ ማስረጃዎችን መያዝ እና ከተማሪዎች የደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ ውሳኔ ይግባኝ ባዩ ያልተስማማበትን በዝርዝር መግለጽ አለበት። ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካያቸው ማስረጃውን መመርመር እና የተማሪዎች የደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ ውሳኔ በመደገፍ ወይም በማሻሻልና እንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ የመፍትሄ ሀሳቦችን በማቅረብ የመጨረሻ የጽሑፍ ሪፖርት ያቀርባሉ። የዋና ተቆጣጣሪው ወይም የተወካዩ ውሳኔ መጨረሻ ይሆናል።

**የውጭ ኤጀንሲዎች**

የርዕስ /Title/ V (ዘር፣ ብሔር)፣ የርዕስ (Title) IX (ፆታ)፣ ወይም የክፍል 504/ADA (አካል ጉዳተኛነት) ጥሰቶችን በተመለከተ አቤቱታዎች በቀጥታ ለOffice for Civil Rights, U.S. Department of Education, 1244 North Speer Blvd., Suite 310, Denver, CO 80204. ሊቀርቡ ይችላሉ።

ሕጋዊ ማጣቀሻ፡-

የትምህርት ማሻሻያ ርዕስ IX /Title IX of the Education Amendments/፣ 20 U.S.C. § 1681
የፍታ ብሔር አዋጅ ርዕስ /Title VI of the Civil Rights Act/፣ 42 U.S.C. § 2000d -R1
በዝርያ መረጃ አለማዳላት አዋጅ /Genetic Information Nondiscrimination Act/፣ 42 U.S.C. § 2000ff et seq።
እኩል የትምህርት ዕድሎች አዋጅ /Equal Educational Opportunities Act/፣ 20 U.S.C. §1701-1758
C.R.S. § 2-4-401(13.5)
C.R.S. § 22-32-109(1)(kk)(II)
C.R.S. § 22-32-110(cc) and (dd)
C.R.S. § 22-61-101
C.R.S. § 24-34-301 et seq.
C.R.S. § 24-34-601 et seq.

የማጣቀሻ ቁጥር /Cross Refs./፡-
JB - ከአድሎ የፃ እና እኩል የትምህርት ዕድል
የፀደቀው፡- ኦክቶበር 23 ቀን 2014